# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

10




መስከረም ፲፮ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም.

## ርእሰ አንቀጽ ።

# አጭር ጉዞ ረዥም ጉዞ

ዛሬ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ ሁለት « ተራማጅ » ቡድኖች እንዳሉ ተደጋግሞ ይነገራል ። እንደእውነቱ ከሆነ በታወቁት ሁለት መሥመሮች መሐል ያለው ልዩነት በተራማጆች መሐከል ያለ ልዩነት መሆኑ ካከተመ ብዙ ጊዜ አልፎታል ። የኢትዮጵያ አብዮት ሂደት በሀገሪቱ ያሉትን የፖለቲካ ኃይሎች በሙሉ በሁለት ታላላቅ ጠላት ሠፈሮች እንዲሸጋሸጉ እያስገደዳቸው ነው። ካሁኑ በግልጥ ለማየት እንደሚቻለው ሁለቱ መሥመሮች በሁለቱ ጠላት ሠፈሮች ሚናቸውን እየለዩ ቦታ ቦታቸውን በመያዝ ላይ ይገኛሉ ።

በኢትዮጵያ የመደቦች አሰላለፍ አንፃር ሲታይ የኢሀአፓ መሪዎች ያለአንዳች ጥርጥር ይህንን ቡድን በፀረ አብዮቱ ግንባር ሰልፉን እንዲያሳምር አርገውታል ። ይህ ቡድን መጀመሪያ በአቋም ደረጃ ፤ ከዚያም በድርጅታዊ ትብብር ደረጃ ፤ ከዚያም በኢትዮጵያ ጭቁኖች ላይ በፀረ—አብዮት አመፅ ደረጃ ሙሉ በሙሉ ከመሳፍንትና ቀልባሽ ኃይሎች ጋር የተሰለፈ ለመሆኑ የሚጠራጠሩ ቢኖሩ እጅግ ጥቂቶች ናቸው ።

በአቋም ደረጃ ይህ ቡድን የኢትዮጵያን አብዮት በሚመለከቱ ዋና ዋና ጥያቄዎች ላይ በሙሉ የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ኅብረት ከሚባለው የነአስፋ ወሰንና መንገሻ ሥዩም የቀልባሽ ፋሽስቶች ድርጅት ጋር አንድ ነው ። ሁለቱም የጊዜው ዋና ጥያቄ የሕዝቡ መንቃት ፤ መደራጀትና መታጠቅ ሳይሆን ጊዜያዊ ‘ሕዝባዊ’ መንግሥት ማቋቋም ነው ይላሉ ። ሁለቱም ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትን ፋሽስት ብለው ይጠራሉ ። ሁለቱም የእድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻን ይቃወማሉ ። ሁለቱም የቀድሞውን ፊውዳል ሥርዓትና ኢምፔሪያሊዝምን እንቃወማለን ይላሉ ። ሁለቱም በአሁኑ ጊዜ ፊውዳሊዝምን ፤ ኢምፔሪያሊዝምንና ድርግን የሚዋጋ አንድ የዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ግንባር መቋቋም አለበት ይላሉ ። ሁለቱም የየካቲት ፷፮ ቀንን አዋጅ እንደሌለ ቆጥረው በመሬት በኩል የግል ሀብትን የሚያጸድቅና በአጭር ጊዜ ውስጥ ይህንን አዋጅ ሊቀለበስ የሚቻል የመሬት ፖሊሲ ይከተላሉ ።

በድርጅታዊ ትብብር ደረጃ የኢሀአፓና የኢዲህ አገናኝ ድርጅት ፤ ተራማጅ ጓዶች «የአስፋ ወሰንና መንገሻ ሥዩም የወጣቶች ድርጅት » ብለው የሰየሙት ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን » የተባለው የጥቂት ግልገል ፋሽስቶች ድርጅት ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ይህ የቀልባሽ ወጣቶች ድርጅት በውጭ አገር የኢሀአፓ ተጠሪ ፤ የትግሉ አስተባባሪ ፤ አስተዋዋቂ ፤ ገንዘብ ሰብሳቢ ሆኖ ይሠራል ። ይህን በመመልከት ከስድስት ወራት በፊት ጓዷት ሠናይት በቀለ « አቋም በየፈርጁ » በሚል ርእስ አዲስ ዘመን ላይ ባቀረበችውና የኢሀአፓ መሪዎች በግልጽም ሆነ « በህቡዕ » መመለስ ባልደፈሩት ጽሑፍ መደምደሚያ ላይ የሚከተለውን ጽፋ ነበር ።

« ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን የተባለው ድርጅት ትንሽ ግራ የሚያጋባ ድርጅት ሆኖ አግኝቸዋለሁ ። በአውሮጳ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ጓዶች ሲጠሩት « የአስፋ ወሰንና መንገሻ ሥዩም የወጣቶች ድርጅት » ይሉታል ። እንባቢ እንደተመለከተው እውነትም ነው ። ግን ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ መጽሔቶች አሰራጭ ድጋፍ ሰብሳቢ አስተዋዋቂ --- ባጭሩ በውጭ አገር እንደድርጅቱ ወኪል መስሎ ይሠራል ። ኢሀአፓ ነኝ የሚለው ድርጅት በአድርባይነትም ይሁን በአቋም መስማማት ( ሁለቱም ቢሆን አሳፋሪ ነው !) ከዚህ የአድኃሪ ወጣቶች ድርጅት ጋር « የለሁበትም » ብሎ አንዴም ሲናገር አልተሰማም ። እንዲያውም በየጽሑፉ አብዮታዊ ድርጅት እያለ ያሞጋግሰዋል ። ይህም ስለሆነ አንድ ጥያቄ መጣብን ። ይህ ድርጅት ምናልባት « ፀረ—ፋሽስት ነን » የሚሉ ቡድኖች ሁሉ ለማቋቋም የሚፈልጉት « የኅብረት ግንባር » የመጀመሪያው ጥንስስ ይሆን ?»

ከዚያ ወዲህ በዚህ የግልገል ፋሽስቶች ድርጅት አማካይነት ኢሀአፓና ኢዲዩ በጀርመን አገር ፤ በእንግሊዝና በአሜሪካ የሚያስተባብሩአቸው ድርጅቶች ፤ በጐረቤት አገሮች የሚያካሂዱት የለጋ ኮብላይ ዘማቾች መርሲነሪ ምልመላ ሥራ ፤ የታሠሩ አሪስቶክራቶችንና መሳፍንትን በኢምፔሪያሊስቶች ተጽእኖ ለማስፈታት በምዕራብ አገሮች ያቋቋሙት « የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴ » የተባለው ድርጅት ሁሉ ለዚህ ፀረ—አብዮት ግንባር መሠረት የተጣለ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል ።

ኢሀአፓና ኢዲዩ በአቋምና በድርጅታዊ ትብብር ደረጃ አልተወሰኑም ። በሰፊው ሕዝብ ላይ መሣሪያ ይዞ በማመጽ ደረጃም ሁለቱ ድርጅቶች በአንድነት ተሰልፈዋል ። ባለፈው ሰሞን የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት አንድ መግለጫ በትክክል እንደተናገረው በአሁኑ ጊዜ የሸፈቱ የመሬት ከበርቴዎችና የኢሀአፓ አባላት በየክፍለ ሀገራቱ በጭቁን ገበሬዎችና በፀጥታ አስከባሪዎች ላይ በአንድነት ሆነው ይተኩሳሉ ፤ ይገድላሉ ። በተለይ ባለፈው ሰሞን በወሎ ክፍለ ሀገር ከጭቁን ገበሬዎች ጋር እየተታኮሱ የተማርኩት የኢሀአፓ አባላት ይህ ቡድን ከኢትዮጵያ አብዮት ጋር ለግባበት ተጻራሪ ቅራኔ ቋሚ ምስክሮች ናቸው ።

አንደኛው ለነቃ ለተደራጀና ለታጠቀ ሕዝብ ትግልና በሰፊው ሕዝብ ሠፈር ፤ ሌላው ለነቃ ፤ ለተደራጀና ለታጠቀ ፀረ—ሕዝብ ትግል በመሳፍንቱና በኢምፔሪያሊስቶች ሰፈር ። ትላንት በተራማጅ ኃይሎች መሐከል ይመስሉ የነበሩት የመሥመር ልዩነቶች ዛሬ ይኸው እንደዚህ ቁልጭ ብለው በአብዮትና በፀረ—አብዮት መካከል ያሉ ልዩነቶች ሆነዋል ። ከትላንትና ይልቅ ዛሬ ይበልጥ ግልጥ የሆነውን ያህል ይህ የኢሀአፓ የፖለቲካ ክስረትና ክህደት ነገ የኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ሌሎች የትግልና የድል ምዕራፎችን ሲቀዳጅ ይበልጥ ግልጥ እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው ። የልዩነቶቹን አመጣጥ ፤ አስተዳደግ ፤ የመደብ ይዞታቸውንና በሁለቱ መሥመሮች መሃከል ገና በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ይካሔድ የነበረውን ትግል በጥሞና የተከታተለ ሁሉ ይህ የዛሬው ሁኔታ ጨርሶ አይገርመውም ።

ልዩነቶቹ እንደዛሬ ቁልጭ ብለው በማይታዩበት ወቅት በሁለቱ መሥመሮች መሐከል የተደረገው ትግል ምንም ዓይነት የረባ ልዩነት በሌላቸው ግለሰቦች መሐከል የሚካሔድ የግለሰቦች ሽኩቻ እንጂ የመደቦች ትግል እንደሆነ የተገነዘቡት ብዙ ሰዎች አልነበሩም ። ግን በሁለቱ መሥመሮች መሐከል የተደረገው ትግል መደባቸውን ከድተው ለወዝአደሩ በቆሙ አብዮታውያንና ከአብዮቱና ከሰፊው ሕዝብ ጋር ለመራመድ የቆረጠው ግራ ክንፍ ንዑስ ከበርቴ በአንድ በኩል ከሕዝብና ከአብዮት በፊት በአቋራጭ ሥልጣን ኮርቻ ላይ ለመውጣት ሲያደባ የቆየው የቀኝ ክንፍ ንዑስ ከበርቴ ክንፍ በሌላ በኩል እንደነበር ግልጥ ነው ።

ልዩነቶቹ አሁንም ሆነ ገና በጥንስሳቸው በአብዮቱ ሂደትና በተራማጆች ተግባር ላይ ነበሩ ። በአንድ በኩል የአብዮት ጉዞ ረዥምና የተወሳሰበ ነው ። ከግቡም የሚደረሰው የአብዮቱ ባለቤት የሆነው ሰፊው ሕዝብ ነቅቶ ፤ ተደራጅቶና ታጥቆ ትግሉን ሲያካሂድ ነው የሚለው አዝማሚያ ነበር ። ከዚህ አቋምም በመነሣት ይህ መሥመር የተራማጆች ተግባር ራስን በቶሎ አደራጅቶ ሰፊውን ሕዝብ ማንቃትና ማደራጀት ነው በሚል ለዚህ አድካሚና ትዕግሥት የሚጠይቅ የትግል ጉዳና ተሠማራ ። ይህንንም መሥመር መከተሉን በግልጽ ስላስታወቀ የዚህ መሥመር ተቃዋሚዎች አብዮታውያንን «ረዥም ጉዞኞች» የሚል የማሽሟጠጥ ስም አውጥተውላቸው እንደነበረ ይታወሳል ።

በሌላ በኩል ደግሞ የአብዮት ጉዞ ረዥምና አታካች መሆኑን በመካድ ፤ የአብዮት ባለቤት ሰፊው ሕዝብ መሆኑን ባለመገንዘብ ጥቂት ፋኖዎችን አስታጥቆ የፊውዳሉን ሥርዓት መገርሰስና ሥልጣን መያዝ ይቻላል የሚል ከሕዝብና ከአብዮት በፊት በአቋራጭ ለሥልጣን የቆመ የቀኝ ክንፍ ንዑስ ከበርቴ ቡድን ተሰለፈ ። አብዮታውያን ይህንን ሠፈር ፤ ይህንን ለጭቁኖች የሌለ አቋራጭ እሳያለሁ እያለ በትግሉ የሚያላግጠውን ወገን «የአጭር ጉዞኞች» ሠፈር ብለው ሰየሙት ።

ይህ ሠፈር እርግጥ ከየካቲት በፊት ጥቂት ፋኖዎችን አሠማርቶ «ሕዝባዊ ጦር» ለማለት ሲቃጣው ፤ ከየካቲት በኋላ ደግሞ ወደሌላው ጫፍ ተወርውሮ «ሕዝባዊ ምርጫ» ብሎ ሲያወናብድ አቋም የቀየረ ይመስላል ። ግን መደብ ዓላማው ከቀድሞው አልተቀየረም ። ትላንትም ሆነ አሁን በዓመፅም ሆነ በምርጫ የዚህ ቡድን ዓላማ ከሕዝብና ከአብዮት በፊት በሕዝብና በአብዮት ስም ሥልጣን ኮርቻ

ላይ ፊጥ ለማለት እንደሆነ ፤ በተለይ ከመስከረም ሁለት ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ጀምሮ እኝኝ ብሎ የያዛት «የጊዜያዊ (ሕዝባዊ) መንግሥት» መፈክሩ ቁልጭ አድርጋ ታጋልጠዋለች ።

የዚች የሥልጣን ባቋራጭ መፈክሩ መክሸፍና የኢትዮጵያ አብዮት አዳዲስ ድሎችን እየተጐናጸፈ መሔድ ፤ ለዚህ ቡድን ክስረትና ክህደት ዋና ምክንያቶች መሆናቸው ግልጽ ነው ። የቀኝ ክንፍ ንዑስ ከበርቴው ቡድን ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ «ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት የቀልባሾች መፈክር ነው» ብሎ ከተነሣበት ወቅት አንሥቶ ፤ በሕዝብና በአብዮት ስም ፤ በአቋራጭ ሥልጣን ላይ የመደላደሉ ተስፋ ጨርሶ ወድሞበታል ። ሰፊው ሕዝብ በንቃት ፤ በድርጅትና በትጥቅ እንጂ በሌላ በምንም ዘዴ ሥልጣንን ለመያዝ እንደማይቻል ነቅቶ «አስታጥቁኝ» በማለት ላይ ነው ። በዚህ ልክ ደግሞ የቀኙ ክንፍ ንዑስ ከበርቴ በአብዮቱ ሠፈር ሚናውን ጨርሷል ። ካሁን ወዲያ ይህ በአብዮቱ ተተፍቶ የታለፈ መደብ ፀረ አብዮት የሆነ ጥቅሙን ለማረጋገጥ ሰፊውን ሕዝብ ማወናበድ ከቶ አይቻለውም ። ሰፊው ሕዝብ እንዳይነቃና እንዳይደራጅ ይህ ቡድን ከመፀነሱ ጀምሮ ይጠነሰስ የነበረው አሻጥር ተራ በተራ ወድሟልና ! ።

በአብዮትና በሰፊው ሕዝብ ስም ማወናበድ ባከተመበት ሁኔታ ይህ ከሀዲ ክንፍ የሚቀረው ከፀረ አብዮቱ ሠፈር በግልጽ ተደባልቆ ጥቅሙን ለማስከበር መታገል ነው ። በዚህ የአብዮት ሂደት ተንሸራትቶ የአድኃሪ ኃይሎች «ተራማጅ ኮከብ» ለመሆን የበቃው ኢህአፓ ሥልጣንን ባቋራጭ ለመያዝ ትላንት ጥቂት ፋኖዎችን አሠማርቶ «ሕዝባዊ ጦር» ይል ነበር ። ከየካቲት ወዲህ ደግሞ ይህንን የትጥቅ አቋራጭ እንዳልነበር ረስቶ «ሕዝባዊ ምርጫ» የሚል አቋራጭ አግኝቶ ለጥቂት ጊዜ አብዮቱን ለመግታት አመቺ የሆነች መፈክር ያገኘ መስሎት ነበር ። ይቺም መፈክር በቀልባሽነቷና በአድኃሪነቷ ተጋለጠች ። የቀረው ጠቅልሎ ወደመሳፍንቱ መግባትና በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ በፊውዳሉ ሥርዓት ላይ አሰልፋለሁ ይላቸው የነበሩትን «ፋኖዎች» ዛሬ ከፊውዳሉ ሥርዓት ርዝራዦች ጋር ሆኖ በጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ማሰለፍ ብቻ ነው ። ስለሆነም ከሀዲው የቀኝ ክንፍ ንዑስ ከበርቴ ቡድን አሰልፌያለሁ የሚለው «ሕዝባዊ ሠራዊት» የኢትዮጵያ ጭቁኖች በያለበት ካሰለፉት ከጭቁን ገበሬዎች «ሕዝባዊ ሠራዊት» ጋር ከመታኮስ ደረጃ የደረሰው ፤ አብዮቱ በንቃት ፤ በድርጅትና በትጥቅ ጐዳና እየገፋ ለኢህአፓና ለቀልባሽ መፈክሮቹ ምንም ዓይነት ሌላ መፈናፈኛ ስላሳጣቸው ነው።

የሆነ ሆኖ የኢህአፓ እንደዚህ መጋለጥና በወዝ አደሩ ፤ በአርሶአደሩ ፤ በመለዮ ለባሹ ፤ በተራማጅ ወጣትና በጠቅላላው በአብዮታዊ ኃይሎች መታለፍ የቀኝ ክንፍ ንዑስ ከበርቴ ፀረ—አብዮት ሚና አከተመ ማለት አይደለም ። የሰፊውን ሕዝብ የንቃት ደረጃ ፤ እንደዚሁም የኢትዮጵያን ሐቀኛ ተራማጆች ለመራራ ትግል ዝግጁነት ባለመገንዘብና በመናቅ የኢትዮጵያን ቀኝ ክንፍ ንዑስ ከበርቴ መደብ በንዝኅላልነት ብዙ በቀላሉ ያጋለጡት ስሕተቶችን ፈጽሟል ። ነገር ግን ከትግሉ እሱም የበኩሉን ተምሯልና መልክና ገጽታ ለውጦ አሁንም በሠርጎ ገብነቱ ለመቀጠል እንደሚፍጨጨር ፤ ስም ለውጦ ፖለቲካ የለወጠ መስሎ እንደሚመጣብን ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው ። ነገር ግን በትግሉ ውስጥ ጭቁኖች ከትግላቸው ይማራሉና ፤ ግንባር ቀደም ተራማጆችም ሠርጎ ገቦችን እያጋለጡ የሰፊውን ሕዝብ ሠፈር አብዮታዊ ጥራት ለመጠበቅ ነቅተው ይጠባበቃሉና ሠርጎ ገቦች የያዙትን ገጽታ ቢይዙ የደረቡትን ካባ ቢደርቡ መጋለጣቸው አይቀርም ። ለዚህ ማርክሲስቶችና ሌሎች ተራማጅ ኃይሎች ትላንትም ሆነ ዛሬ የተሰለፉበትን የነቃ ፤ የተደራጀና የታጠቀ ሕዝብ ትግል መፈክራቸውን ከመቼውም ይበልጥ አንግበው ወደፊት መግፋት አለባቸው ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች ከቀኝ ክንፍ ንዑስ ከበርቴው አንሥተው እስከ መሳፍንቱ ድረስ ጥቃቅን ልዩነቶቻቸውን አቻችለው ፀረ ሕዝብ ግንባር በማስተባበር ላይ ናቸውና የኢትዮጵያ ወዝአደሮች አርሶ አደሮች ፤ መለዮ ለባሾች ፤ ተራማጅ ተማሪዎችና ምሁራን ፤ ነጋዴዎችና ሌሎች አገር ወዳድ ኃይሎች በሙሉ እነሱም በበኩላቸው ልዩነቶቻቸውን አቻችለው ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ለመፍጠር መታገል አለባቸው ። የድሉ ዋስትና ይኸው ነው ።

ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው ።
አብዮታዊት ኢትዮጵያ ።